# ልሳን

በአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ

በዚህ ጽሑፍ መሠረት ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት ነው /የሐዋ. ሥራ 2÷4/። በልሳን መናገር ማለት የሰው ልጆች በሚሰሙትና በሚናገሩት ቋንቋ መናገር ማለት ነው። እንዲሁም በአዲስ ልሳን መናገር ማለት በአዲስ ቋንቋ መናገር ማለት ነው /ማር.16÷17/ ። በአዲስ ቋንቋ መናገር ማለትም ተወልደው ባላደጉበት፣ ወጥተው ወርደው ባልተማሩበት ቋንቋ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት መናገር ማለት ነው።

ልሳን ቁጥር ስፍር ከሌላቸው መንፈስ ቅዱስ ከፍሎ ለክርስቲያኖች ከሚሰጣቸው ስጦታዎች አንዱ ነው /1ኛ ቆሮ 12 ÷10/። የልሳን ጸጋ በሐዲስ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ለሐዋርያት ነው። እለቱም መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በወረደበት በጰንጠቆስጤ(በሃምሳኛው) ቀን (በበዓለ ሃምሳ) ነው /የሐዋ 2÷1/። የመጀመሪያውንና እውነተኛውን ልሳን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። “ለሁሉም(በሐዋርያት) መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስ ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።

ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤ ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፥ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ። ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ፦ እነሆ እነዚህ ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?

የጳርቴና የሜድ ፥ የኢላሚጤም ሰዎች፥ በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጶዶቅያም በጳንጦስም በእስያም፤ በፍርግያም በጵንፍልያም በግብጽም በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር፤ በሮሚም የምንቀመጥ፥ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን የቀርጤስና የዓረብ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻቸው ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። ሁሉም ተገረሙና አመንትተው እርስ በእርሳቸው እንኝ ይህ ምን ይሆን? አሉ። ሌሎች ግን እያፌዙባቸው ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ።

ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ እናንተ የይሁዳ ሰዎች በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ። ለእናንተ እንደመሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው። “እግዚአብሔር ይላል፥ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ...የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል” /የሐዋ ሥራ 2÷1-21/።

እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በሌላ ልሳን መናገር ማለት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የሰው ልጆች በሚሰሙበትና በሚናገሩበት ልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር ማለት እንደሆነ በዚሁ ምዕራፍ በግልጥ ተረድተናል። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር የዕብራይስጥ ቋንቋ ብቻ ለሚያውቁ፥ ለአይሁድ ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮ እንደመለፍለፍ ነበር። መንፈስ ቅዱስ የማያውቁትን ቋንቋ እንደ ሐዋርያት አልገለጠላቸውምና።

በበዓለ ኀምሳ እለት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ (ስጦታ) ሐዋርያት በልዩ ልዩ ልሳን (ቋንቋ) ወንጌልን በሰበኩ ጊዜ ግን አድማጮች ከዕብራይስጥ በቀር ሌላ ቋንቋ አይችሉም። ሆኖም ሐዋርያት በእያንዳንዳችን ቋንቋ ወንጌልን እንዴት ሊሰብኩ ቻሉ? በማለት ከመገረማቸው በላይ ይህን ተአምር በማየት በአንድ ቀን 3000 (ሦስር ሺ.ህ) ሰዎች ተጠምቀዋል /የሐዋ. ሥራ 2፥41.። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በልሳን (የሰው ልጅ በሚሰሙበት ቋንቋ) መናገር ለማያምኑት ይጠቅማል፥ ካመኑት ይልቅ ለማያምኑት እንደምልክት ሆኖ እንዲያምኑ ያደርጋልና /1ኛ ቆሮ 14፥22/።

በልሳን (በአዲስ ቋንቋ) መናገር በሐዋርያት ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ቁጥር 17 እንደምንገዳው ላመኑትና ለተጠመቁት ከሚሰጧቸው ጸጋዎች አንዱ በአዲስ ቋንቋ መናገር እንደመሆኑ መጠን አምነው ከሚጠመቁት ምእመናን አንዳንዶቹ ይሰጣቸው ነበር። ለዚህም የሚከተለውን እንመልከት። “ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፥ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ። ሰዎቹም ሁሉ አሥራ ሁለት ያህሉ ነበር” ይላል /የሐዋ. ሥራ 19፥5-7/።

ቅዱስ ጳውሎስም፥ “በልሳኖች ከመናገር አትከልክሉ” ይላል /1ኛ ቆሮ 14፥39/። የልሳን ጸጋ ተሰጠኝ ተብሎ በጉባኤ መካከል ስፍር ቁጥር የሌለው ቋንቋ መናገር እግዚአብሔር የማያውቀው ቋንቋ ስለሌለ ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሙሉ ግንኙነት ይኖረዋል እንጂ ለጉባኤው ሙሉ በሙሉ እንደማይጠቅም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፦ “በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም የሚያስተውለውም የለምና” /1ኛ ቆሮ. 14፥2/።

በልሳን(በልዩ ልዩ ቋንቋ) የመናገር ጸጋ የተሰጠው ሰው በጉባኤ መካከል በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገር ከሆነ በጉባኤው የተሰበሰቡት ሰዎች በሚሰሙበት የወል ቋንቋ መተርጎም እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል። እንዲህ ሲል፦ “ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ” /1ኛ ቆሮ. 14፥13/። በልሳን (በተለያዩ ቋንቋዎች) የመናገር ጸጋ ተሰጥቶት በጉባዔ የተሰበሰቡት ምእመናን ሁሉም እንዲሰሙ የጋራቸው ወደሆነው ቋንቋቸው የመተርጐም ጸጋ ካልተሰጠው ደግሞ በ 1ኛ ቆሮ ምዕራፍ 12 ቁጥር 10 ላይ እንደተገለጠው ሌላው ብዙኃኑ ወደሚሰሙት የወል ቋንቋ እንዲተረጐምለት መደረግ አለበት።

ይህም የግእዝን ቋንቋ እያወቅንና ግእዙን እያነበብን ቅኔ ባለማወቃችን ወይም የግእዝን ትርጉም ባለመረዳታችን ምክንያት ግእዙን ወደ አማርኛ የሚተረጉም ሌላ ትርጓሜ እንደሚያስፈልገን እንደ አንዳንድ ሰዎች ማለት ነው። ግእዝን የምናነብ ሰዎች ሁላችንም በትክክል የመተርጐም ዕውቀት የለንምና። በልሳን ወይንም በልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር በጉባዔ ከተሰበሰቡት ለብዙዎች ቢገለጥላቸው መናገር የሚገባቸው ግን ተራቸውን ጠብቀው ሁለት ቢበዛ ሦስት ሰዎች ብቻ መናገር እንደሚገባቸውና የመተርጐም ጸጋ የተሰጠውም እነርሱ የሚናገሩትን ልዩ ልዩ ቋንቋ ብዙኃን ወደሚሰሙበት የጋራ (የወል) ቋንቋ እንዲተረጉምላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል /1ኛ ቆሮ 14፥27/።

ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ ስለልሳን ብዙ ከተናገረ በኋላ በእውነት ላመኑ ክርስቲያኖች የልሳን ወይም የቋንቋ ጋጋታ ምንም እንደማይጠቅም እንዲህ ሲል ተናገረ፦ “እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም። ትንቢት (ማስተማር) ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም። እንግዲህ ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ አብደዋል አይደሉምን? ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳል፤ በሁሉም ይመረመራል፥በልቡም የተሰወረ ይገለጣል ፥ እንዲሁም እግዚአብሔር በእውነት በመካከላቸው ነው ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል” /1ኛ ቆሮ 14፥22-25/።

በዚህ ምንባብ ውስጥ (ቁጥር 24) “ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን” የሚለው ሁሉም ወይም በጉባዔው የተገኙት ሰዎች በሙሉ በሚሰሙበት በጋራ ቋንቋቸው ወንጌል ቢያስተምሩ ማለት እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። የወንጌሉ ትምህርት “ትንቢት” መባሉም ላላመኑት ብታምኑና ብትጠመቁ ትድናላችሁ፤ ላመኑት ደግሞ መድኅን ክርስቶስ ዳግም ይመጣል፤ የዘለዓለም ሕይወት መንግሥተ ሰማያትን እንወርሳለን። ስለዚህ ሁል ጊዜ ዝግጁ ሆነን እንጠብቅ ተብሎ በትንቢት (በይሆናል) በመልክ የሚሰብክ ስለሆነ ነው።

ስለ ልሳን የቅዱስ ጳውሎስን ምክር ስንመለከት፦ “ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች (በቋንቋዎች) እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፥ ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ” /1ኛ ቆሮ 14፥18-19/። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እልፍ ቃላት በልሳን ከምናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ መናገርን እወዳለሁ ሲል ገና ጸጋው ተሰጠኝ ብዬ በጉባዔ የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉም በማይሰሙት በልዩ ልዩ ቋንቋ እየተናገርሁ ጊዜዬን ከማባክን በአእምሮዬ (እኔ በማውቀውና ሌሎችም በሚያውቁት) በአንድ ቋንቋ አምስት ቃላት ብናገር በጉባዔ የተሰበሰቡት ይጠቀማሉ ማለት ነው። በአእምሮዬ ስል በማውቀው በእውቀቴ፤ በሚያውቁት በእውቀታቸው ለማለት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ እንዲህ ይላል። “ወንድሞች ሆይ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ። በአእምሮ የበሰላችሁ ሁኑ” /1ኛ ቆሮ 14፥ 20/።

በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ሲል በእውቀት እንደ ሕፃናት አትሁኑ ለማለት እንደሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ሕፃናት ምንም የሚያውቁት ነገር የለምና። "በአእምሮ የበሰላችሁ ሁኑ" ሲልም በእውቀት የበሰላችሁ ሁኑ ማለት ነው። በሌላ በኩል አእምሮ ማለት ማስተዋል ይሆናል። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ እልፍ ቃላት ሰው በማያስተውለው (በማያውቀው) ቋንቋ ከምናገር ሰው በሚያስተውለው (በሚያውቀው) ቋንቋ አምስት ቃላት መናገር ይጠቅማል ሲል፥ በልሳን ከመናገር በአእምሮ መናገር ይጠቅማል ካለው ጋር አንድ ነው።

አንባቢያን ሆይ! ስለ ልሳን በመጠኑም ቢሆን ተመልክተናል። ልሳን ማለት ቋንቋ እንደሆነና በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በሌላ ልሳን (በአዲስ ቋንቋ) መናገር ማለት ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ተወልዶ ባላደጉበት፣ ተምረው ባላወቁበት የሰው ልጆች የሚናገሩበትን ቋንቋ ሁሉ ማወቅና መናገር ማለት እንደሆነ በሐዋ. ሥራ 2፥1-17 ተረድተናል። ነገር ግን ይህን የመሰለው እውነተኛውና መጽሐፍ ቅዱሳዊው የልሳን ጸጋ በዘመናችን አለ ማለት የሚቻል ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተጽፎ የምናገኘውን ይህንን ጸጋ ለመቀበል የተዘጋጀ ሕይወት ያለው ሰው እምብዛም ነው። ይህ ለምን ሆነ እንል ይሆናል። ለዚህም መልስ የተለያዩ ክፍሎች የየራሳቸውን አስተያየት ይሰጣሉ። ከእነዚህ መካከል ሁለቱን ግምቶች እንደሚከተለው አቅርበናል።

1. ሀ) "በዓለም ምናልባት ቁጥር የሌለው የቋንቋ ዓይነት ይኖራል። ቋንቋ የሌለው ሕዝብ የለም፥ እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ እሆናለሁ፥ የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል" /1ኛ ቆሮ 14፥10-11/።

   ለ) "እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም" ይላል /1ኛ ቆሮ 14፥22/። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት በጉባዔ ቆሞ በዓለም ያሉ ሕዝብ ሁሉ የሚናገሩባቸው ቁጥር ሥፍር በሌላቸው ቋንቋዎች መናገር ጊዜን ማባከን እንጂ ማኅበሩን አያንጽም። ምክንያቱም ማኅበሩም ሚታነጸው በጉባዔ የተሰበሰቡት ሁሉም በሚሰሙት በወል ቋንቋቸው ወንጌል ሲሰበክ ነውና። ደግሞም ቅዱስ ጳውሎስ የልሳን (የቋንቋ) ብዛት ለሚያምኑ አያስፈልግም ስላለ በዚህ ምክንያት ይሆናል የሚሉ መልስ አለ።

2. መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የልሳን ጸጋውን ያፈሰሰው አንድ ልብ በሆነች መለያየት በሌለባት ቤተ ክርስቲያን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መረጃውም እንዲህ ይላል፦ "በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው። እየተጕረደ እንደሚሄድ እሳት የተከፋፈሉ የእሳት ላንቃዎች ታዩአቸው፥ በእያንዳንዳቸውም ላይ አደረባቸው። ሁሉም ኃይል የሚሆናቸውን መንፈስ ተሞሉ፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች (ቋንቋዎች) ይናገሩ ጀመር። ... እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ፥ ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ፥"እነሆ እነዚህ

የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?"ይላል /የሐዋ. 2፥ 1-9/።

መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው። ጸጋው (ስጦታው) ግን ብዙ ነው። /1ኛ ቆሮ 1፥4/። መንፈስ ቅዱስ ብዙ ከሆነው ጸጋው ለመስጠት አንድ ልብ የሆኑ መለያየት፣ መነቃቀፍ፣ ክርክር በመካከላቸው የሌለ ክርስቲያኖችን ይፈልጋል። ሆኖም ግን መለያየት፣ መነቃቀፍ፣ ክርክር በዚህ ዘመን ጐልቶ ይታያል። በመለያየት መካከል ደግሞ የመንፈስ ጸጋ የለም።፡

ስለዚህ በዚህ ዘመን ምናልባት የልሳን ጸጋ የተቋረጠው በክርስቲያኖች አንድ ልብ አለመሆንና መለያየት ምክንያት ነው የሚል መልስ አለ። በተረፈ ግን ልሳን በዚህ ዘመን የተቋረጠበት ምክንያት የልሳን (ቋንቋ) ወይም የጸጋ ሁሉ ባለቤት የሆነ ልዑል እግዚአብሔር እንተዋለን። የእርሱን ምስጢር ማንም አያውቅምና።/1ኛ ቆሮ2፥11/። በዘመናችንም በልሳን እንናገራለን የሚሉ አሉ። ለመሆኑ ይኸ አባባላቸው እውነት ይሆን?

በዘመናችን በልሳን እንናገራለን የሚሉና በዚህም እጅግ የሚመኩ አሉ። ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው አማናዊ ልሳን ጋራ ሲነጻጸር መጽሐፋዊ ያልሆነና ፍጹም ሐሰት ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላን ብለው የሚናገሩት አዲስ ልሳንም የሚሉት በዓለም ካሉት ቋንቋዎች አንዱን እንኳን የማይመስልና የቋንቋ ጠባይም ስለሌለው ነው።

ሐዋርያት እኮ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በሌሎች ልሳኖች (ቋንቋዎች) ሲናገሩ በጉባዔ የተሰበሰቡት ሁሉ "በእያንዳንዳችን ቋንቋ ነው የሚናገሩት" ሲሉ መስክረውላቸዋል። ይህ የዘመናችን ልሳን ነኝ ተብዬ ቋንቋ የእኔ ነው ብሎ የሚመሰክርለት ባለመኖሩ ምን እንበለው?ማታለያ?

በእርግጥ አንዳንዶቹ የመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ ነው ይላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ የመላእክት ቋንቋ ነው ይላሉ። መልካም እነሱ የሚሉትን አምኖ ለመቀበል በግድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መኖር አለበት። ሐዋርያትና የመጀመሪያዎቹ በልሳን ተናጋሪ ክርቲያኖች ከሰው ልጆች ቋንቋ ውጭ በመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ በመላእክትም ቋንቋ ተናገሩ የሚል አለ ወይ? ካለስ እስኪ መረጃው? አንዳንዶች ደግሞ እንዲህ ይላሉ፥ በ1ኛ ቆሮ 14፥10 "ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጐም ይሰጠዋል" ይላልና ምንም እንኳ እኛ ሰው በማይሰማው ቋንቋ ብንናገር የመተርጐም ጸጋ የተሰጠው ስለሚተረጉመው ችግር የለም ይላሉ።

መልካም "የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው" እንዲሉ በፈለጉት ዓይነት የኮድ ቋንቋ ተንተባትበው ብዙኃኑ ወደሚሰሙት ቋንቋ ተርጉመው ሰዎች ወደ ንስሐ የሚመለሱ ከሆነ ባልተቃወምንም ነበር። ነገር ግን እኛን ያሳሰበን ነገር ቢኖር በልሳን ከመናገር በፊት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሰበብ የሚከሰተው መንቀጥቀጥ፥ የሚታየው የአእምሮ መረበሽና መጮኽ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያስደስታል፥ ሰላምን ይሰጣል እንጂ አያስጨንቅም፥ አያንቀጠቅጥም፥ አእምሮንም አይለውጥምና

ይኸም ዓይነት ድርጊት ወደ ክፉ መንፈስ ያዘነበለ በመሄዱ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል እንላለን። መጽሐፍ ቅዱስ "መንፈስን ሁሉ አትመኑ ይላልና" /1ኛ ዮሐ. 4÷1/።

እንደ እውነቱ ከሆነ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 10 ላይ ለአንዱ የመተርጐም ጸጋ ይሰጠዋል ሲል ለምሳሌ ያህል በአገራችን ብዙ ቋንቋዎች አሉ፤ ስለዚህ በጉባዔ የተሰበሰቡት ለአንዱ እነዚህን ቋንቋዎች የመናገር ጸጋ ቢሰጠው የመተርጐም ጸጋ የተሰጠው ደግሞ እነዚህን ብዛት ያላቸውን ቋንቋዎች ብዙኃኑ ለሚሰሙት ለምሳሌ ያህል ወደ አማርኛ ወይም ወደ ትግርኛ ወይም ወደ ኦሮምኛ እየተረጐመ የወንጌሉን ቃል ማሰማት ማለት ነው።

የልሳን ጸጋ በተለይ በብዛት መሥራት ያለበት በዚህ በመጨረሻው ዘመን ነው። ብለው የሚከራከሩት እንደመገኛ አድርገው የሚያቀርቡት ጥቅስ እነሆ፦ "እግዚአብሔር ይላል÷ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል÷ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ÷ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ" ይላል /የሐዋ. ሥራ 2÷27/።ስለዚህ ዛሬ እኛ በልሳን የምንናገረው መንፈስ በጉባኤያችን እየፈሰሰ ነው። ኦርቶዶክሳውያንም በመንፈስ ተሞልተው በጉባዔያቸው በልሳን የማይናገሩት በጉባዔያቸው መንፈስ ስለማይፈስና ትክክለኛ እምነት ስለሌላቸው ነው ይላሉ።

እስኪ በቅድሚያ "በመጨረሻው ቀን" የሚለውን እንመልከት፤ አንባቢያን ሆይ ይህን ቃል ከነቢዩ ኢዩኤል ጠቅሶ የተናገረው ቅዱስ ጳውሎስ ነው።፡የተናገረበትም እለት መንፈስ ቅዱስ በወረደበት እለት ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በሌሎች ልሳኖች በተናገሩበት ሰዓት በበዓለ ኀምሳ ነው። የተናገረበትም ምክንያት ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በሐዋ. ሥራ 2÷5 -15 እንደተገለጠው በዐረብኛ÷ በግሪክኛ÷ በእስያ÷ በሮማይስጥና በሊቢያ በመሳሰሉት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሲናገሩ የነዚህ ቋንቋዎች ባለቤቶች ከልዩ ልዩ አገሮች ተሰባስበው እግዚአብሔርን ለማመስገን እንደ ሥርዓታቸው ኢየሩሳሌም ተገኝተው ስለነበርና በየገዛ ቋንቋቸው የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማዳን (ወንጌልን) ስለሰበኩላቸው ተገርመው ÷ ተደንቀውም እነዚህ ሐዋርያት ከዕብራይስጥ በቀር ሌላ ቋንቋ አይችሉም ነገር ግን በእያንዳንዳችን ቋንቋ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንዴት ሊናገሩ ቻሉ? አስደናቂ ነገር ነው በማለት ይህ ምልክት ሆኖላቸው በአንድ ቀን ሦስት ሺህ ሰዎች ሲጠመቁ በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁድ ግን ከዕብራይስጥ በቀር ሌላ ቋንቋ ባለመቻለቸውና ሐዋርያት የሚናገሩትን ልዩ ልዩ ቋንቋ ባለመስማታቸው ሐዋርያትን ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረው ነው የሚለፈልፉት አሉ /የሐዋ. 2÷11-12/። በዚህ ጊዜ ነው ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሥቶ አሁን ከጧቱ ሦስት ሰዓት ነው የሚሰክሩበት ሰዓት አይደለም። ነገር ግን በነቢዩ በኢዩኤል ስለዛሬው ቀን ትንቢት ተነግሮ ነበር።ያም ትንቢት "በመጨረሻው ቀን ሥጋን በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ÷ ወንዶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ" የሚል ነውና አሁን ሐዋርያት ሰክረው ሳይሆን ይህ ትንቢት ወፈጸሙን የሚያረጋግጥ ነው ሲል ተናግሯል።

አሁን እንግዲህ ቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ የወረዱበትን እለትና ሐዋርያት በልሳን የተናገሩበትን እለት የመጨረሻ ዘመን ነውን? አይደለም። ቅዱስ ጴጥሮስ የመጨረሻው ቀን ያለው የዓመተ ፍዳን÷የ ዓመተ ኩነኔን÷ የዓመተ ኃጢአትንና የዓመተ ሞትን መጨረሻ ነው። የፍዳን ዘመን፣ የኩነኔ ዘመን

የኃጢአትና የሞት ዘመን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አክትሞአልና ደግሞም በአዳም በደል ምክንያት ሞትና ኃጢአት የሰው ልጆችን እንደገዙ እንደማይቀሩና መድኅን ክርስቶስ አንድ ቀን በደሙ መፍሰስ እንደሚያስወግዳቸው ተስፋ ስለነበረና ይህም ተስፋ ብዙ ዘመናት አስቆጥሮ ስለተፈጸመ፥ በክርስቶስ ደም ዲያቢሎስና የእሱ የግብር ልጆች ሞትና ኃጢአት ድል የሆኑበትም፥ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በዓለም የብርሃን ሥራውን የጀመረበትን ሰሞን የመጨረሻ ቀን ብሎታል። ለዚህም መረጃ ይሆነን ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ እንዲህ ይላል። "ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ" ይላል/ ገላ 4፥4/። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣበትና የተገለጠበት ዘመን የዓለም የመጨረሻ ዘመን ነው ማለት አይደለም። የመዳን ተስፋ የተፈጸመበት፥ የገነት በር የተከፈተበት፥ ሞትና ኃጢአት ድል የሆኑበት፥ ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን ልጆች የመግዛቱ ዘመን ያከተመበት ማለት ነው እንጂ። አሁን ስላለንበትና ስለ ዓለም እድሜ መጨረሻ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፥ ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትንና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው? አሉት። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፥ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ" /ማቴ 24፥3-6/። "ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ፥ ብዙዎች ያስታሉ፥ ከአመጻም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች" /ማቴ. 24፥11-12/።

"በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ቢላችሁ አትመኑ፥ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ" /ማቴ 24፥ 23-25/። እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል" /ማቴ 24፥13/። ስለ ዓለም የመጨረሻ ዘመን ምልክቶት ማቴዎስ 24 ከቁ.1 እስከመጨረሻ ብንመለከት ይጠቅመናል።

ክርስቲያኖች ሆይ! አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት በጠየቁት መሠረት ስለ ዓለም የመጨረሻ ዘመን የተናገራቸውን ስንመለከት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እየፈሰሰ በእውነተኛ ልሳን መናገር ሳይሆን ከመለያየትና ከፍቅር መቀዝቀዝ የተነሣ ሐሰተኛ መንፈስ ክርስቲያኖችን እንደሚያሳስት (በክርስቶስ ስም) ፤ በዚህ በመጨረሻ ዘመን ይነሳሉ የተባሉትም እውነተኞች መምህራን ሳይሆኑ ሐሰተኞች፤ እውነተኞች ነቢያት ሳይሆኑ ውሸተኞች በስሙ የሚያደርጉት ምልክትና ተ አምራትም ማሳሳቻ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ የሚታለሉበት የክፉ መንፈስ ተንኮል እንደሆነ ነው የተነገረን። እነዚህ ሰዎች በጌታ ዳግም ምፅአትና በፍርድ ቀን ተስፋ የሚያስቆርጥ አስደንጋጭ የመለኮት ቃል እንደሚሰሙ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢትን አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜ ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ" ይላል /ማቴ 7፥22-23/።

የናዝሬቱ ጌታ በኢየሱስ ስም በማለት ይህን ሁሉ ተአምራት ሲያደርጉ ቆይተው ለምን አመፀኞች ተባሉ የሚል ጠያቂ ይኖራል። አመፅ ማለት ትእዛዙን አለማክበር ማለት ነው። ስለዚህ ሰዎች የመጀመሪያ ትእዛዙን አላከበሩምና ከትእዛዙም መጀመሪያ እንዲህ የሚል ነው። "እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ እንድትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት" ዮሐ 15፥12። ይህ ትእዛዝ አልተከበረም እርስ በእርስ መዋደድ የለምና። እርስ በእርስ መዋደድ ቢኖር ኖሮ እንደዚህ መለያየትና ቁጥር ስፍር የሌለው ድርጅት አይፈጠርም ነበር። በአጠቃላይ በመጨረሻው ዘመን እውነተኞች መምህራን፥ እውነተኞች ነቢያት ይነሣሉ ነብሎ በወንጌሉ ቢነገረን ኖሮ በዚህ ዘመን እውነተኞች ክርስቲያኖች እኛ ነን መንፈስ እየፈሰሰልን በልሳን እንናገራለን የሚሉትን ሁሉ በምስጋና በተቀበልን ነበር። ነገር ግን በጊዜው የማሳሳቻ መንፈስ እየተሸከሙ የሚመጡትን ሁሉ የምትቀበልበት እጅ፥ የምናዝልበት ጆርባ የለንምና ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ተሳስታችሁ አታሳስቱ እንላለን።

## ማጠቃለያ

መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የልሳንን (ቋንቋን) ጸጋ የሰጠበት ምክንያት ሐዋርያት በዓለም ተዘዋውረው ሲያስተምሩና ወንጌልን ሲያስፋፉ የቋንቋ ችግር እንዳይገጥማቸውና የወንጌሉ ትምህርት በፍጥነት እንዲስፋፋ የቋንቋ መገለጥ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል / የሐዋ. ሥራ 10፥44-47፤ የሐዋ.ሥራ 11፥15/። ቅዱስ ጳውሎስም በነበረበት ዘመን የነበረው ልሳን ሰው የሚናገረው፣ ሰው የሚሰማው የሚተሮም ነው። የአሁኑ ዘመን ልሳን ግን ማንም የማይሰማው በዓለም ካሉት ሰዎች አንድ እንኳን ተነስቶ የእኔ ቋንቋ ነው ብሎ የማይመሰክርለት ትርጉም የለሽ የውሸት ቋንቋ ነው።ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው።

በዚህ ዘመን ልሳን እንናገራለን የሚሉ ሁሉ እንደ ዋሽንትና ክራር የመሳሰሉት ነፍስ የሌላቸው መሳሪያዎች የመዝሙርን ምስጢር የሚገልጡትን ያህል የማይገልጥና ትርጉም የለሽ በሆነ ከንቱ መለፍለፍ ተታለው ከሚደክሙ እውነትን በመፈለግ ራሳቸውን እንዲያርሙና በዚህ ጉዳይ በእጅጉ እንዲያስቡበት በእግዚአብሔር ስም አደራ እንላለን።

እንግዲህ የተሳሳትን ስህተታችንን አርመን ምግባራችን የተበላሸብን ከተበላሸው ምግባራችን በንስሐ ተመልሰን እረኛው አንድ መንጋውም አንድ የሚሆነበት ጊዜ አለ ይላልና። በአንዲት ጥምቀት፣ በአንድ እምነት፣ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ተመርተን፣ ስለ በደላችን የሞተውን የተነሣውን፣ በክብር ያረገውንና አሁንም ከ እኛ ጋር ያለውን አምላክ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአንድ ልብ፣ በአንድ ቃል በማመስገን የሚመጣውን ተስፋ ወራሾች ለመሆን ያብቃን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር (ሐመር ሚያዚያ 1985)